# ቀልደኛው ዐቢይና የ"ጋብዙኝ?" ሽፍጠኛ ጥያቄው!

ጠቅላይ ሚንስትር (ጠቅላይ ዋና ሹም) ዶ/ር (ሊ.ማ.) ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያውያን በሰሜን አሜሪካ እና በአውሮፓ በየዓመቱ በደመቀ ሁኔታ በሚያኪያሒዱት የስፖርት (የፍን፤ ፍን ሲነበብ ን ትጠብቃለች) በዓል ላይ በእንግድነት ለመገኘት እንዲፈቀድላቸው የ"እባካቹህ ጋብዙኝ?" ጥያቄ በደብዳቤ ማቅረባቸው ተሰምቷል፡፡ የቀረበውን ጥያቄ ተከትሎም የስፖርት ፌዴሬሽኑ (የፍን ነጻ አሥተዳደሩ) ቦርድ (ባለአደራ) በጉዳዩ ላይ ለመምከርና ምላሽ ለመስጠት አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ እንደሆነ ታውቋል፡፡

የአሜሪካውም ሆነ የአውሮፓው ቦርድ (ባለአደራ) "የተሳሳተ ውሳኔ ያስተላልፉ ይሆናል!" የሚለው ሥጋቴ በማየሉ ነው ይህችን ጽሑፍ ለመጻፍ የተገደድኩት፡፡ ሥጋቴ የመነጨው ከወያኔ ነውረኛ ማንነትና ወራዳ ተግባር ነው፡፡ እንዴት? ቢባል ወያኔ በጀርባ በኩል ሔዶ ዐቢይ ሊጋበዝ እንደሚችል ሳያረጋግጥ ጥያቄውን ያቀርባል ብየ ላምን አልቻልኩም፡፡

በተለይ ደግሞ ወያኔ ከዚህ ቀደም የሰሜን አሜሪካውን የስፖርት ፌዴሬሽን (የፍን ነጻ አሥተዳደር) ለመቆጣጠር ወይም በእጁ ለማስገባት ብዙ የደከመና ቀላል የማይባል ችግርም የፈጠረ መሆኑ ሲታሰብ ወያኔ ከዚህ የስፖርት ፌዴሬሽን (የፍን ነጻ አሥተዳደር) ጋር ግንኙነት መፍጠር ሲያስብ ውጤቱ ወይም ምላሹ ያማረ እንዲሆንለት ምን ያህል ዝግጅትና ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚችል እንዲሁ መገመት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ወያኔ አስቀድሞ የቤት ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ ነው ጥያቄውን በአንባሳደሩ (በእንደራሴው) ካሳ ተክለብርሃን በኩል በደብዳቤ እንዲቀርብ ያደረገው የሚል ግምት አለኝ፡፡ እናም አብላጫውን የቦርድ (የባለአደራ) አባላትን ድምፅ ዶላር ረጭቶ፣ ወይም በሌሎች ጥቅሞች ደልሎ ገዝቷል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ይሄ ግምቴ ትክክል የሚሆነው ባለአደራው ተሰብስቦ ዐቢይ በዓሉ ላይ እንዲገኝ በድምፅ ብልጫ ከፈቀደ ወይም ከወሰነ ነው፡፡

ዐቢይ እንዲገኝ ካልፈቀደ ግን ወያኔ የባለአደራ አባላትን በዶላር ወይም በጥቅም ለመደለል ያደረገው ጥረት ሳይሳካለት ቀርቶ የባለአደራ አባላቱ ለሕሊናቸው ለሀገርና ለሕዝብ ታማኝ በመሆን መወሰናቸውን ያረጋግጣል፡፡ አንድ ነገር ግን እርግጠኛ ልትሆኑ ትችላላቹህ፡፡ ወያኔ በጎን የባለአደራ አባላትን ለመደለልና ለማግባባት ጥረት ሳያደርግ ጥያቄውን ሊያቀርብ እንደማይችል፡፡

ወያኔ ጥያቄውን ከማቅረቡ በፊት የባለአደራ አባላትን በጎን ለማነጋገር የሚገደድበት ሌላኛው ምክንያት ፌዴሬሽኑ (ነጻ አሥተዳደሩ) በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ፌዴሬሽኑን (ነጻ አሥተዳደሩን) ከማንም ያልወገነ ለማድረግ በማሰብ ፖለቲከኛን በክብር እንግድነት መጋበዝ እንደሌለበት የሚከለክል አንቀጽ ያለ በመሆኑ ነው፡፡

ይሄንን አንቀጽ ወያኔ ስለማያውቀው ነው ጥያቄውን ያቀረበው እንዳይባል ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በክብር እንግድነት ሊጋበዙ ከታሰቡ በኋላ በዚህ አንቀጽ ምክንያት ሳይጋበዙ የቀሩ እንግዶች መኖራቸውን ወያኔ አሳምሮ ያውቃል፡፡ ይሄን እያወቀ ጥያቄውን

ማቅረቡ መተዳደሪያ ደንባቸው ቢከለክልም ጥያቄውን በልዩ ሁኔታ (in exceptional case) ለማስተናገድ መታሰቡን ያመለክታል፡፡

"ዐቢይ ይሄንን መድረክ ለምን ፈለገው?" ብለን መጠየቅ ያለብን ይመስለኛል፡፡ ሁለት ዐበይት ምክንያቶች አሉ፡-

1ኛ. ዋነኛው ምክንያት በዳያስፖራ (በሀገረ ግዩራን) ያሉ ኢትዮጵያውያን ሰላማዊ ሰልፍ እየወጡና በሌሎችም መንገዶች በየጊዜው በወያኔ ላይ ተቃውሞ ሲያሰሙ የቆዩ እንደመሆናቸው መጠን ይሄም ጉዳይ ግዩራን ኢትዮጵያውያን ባሉባቸው ሀገራት መንግሥታት ዘንድ በሚገባ የሚታወቅ ጉዳይ እንደመሆኑና በዚህም ምክንያት በወያኔ እና በእነኝህ መንግሥታት መሀከል የግንኙነት መሻከር ስለተፈጠረ ዐቢይ በዚህ በዓል ላይ በክብር እንግድነት እንዲገኝ መደረጉ ለእነኝህ ሀገራት መንግሥታትና ባጠቃላይ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሚሰጠው ትርጉም ለወያኔ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ስለሆነ ነው ወያኔ ዐቢይ እዚያ እንዲገኝ የፈለገበት አንደኛው ምክንያት፡፡

2ኛ. ሁለተኛው ፋይዳ ደግሞ ዳያስፖራውን (ግዩራኑን) አግባብቶ ደልሎ ከወያኔ ጎን እንዲሰለፍ ለማድረግ፣ አንድነቱን ለመከፋፈል፣ በዳያስፖራው ያለውን ተቃውሞ ማምከን እንኳ ባይቻል ለመፈረካከስ በማሰብ ነው፡፡

ዐቢይ በእነዚህ በዓላት መድረኮች መገኘት ቢችል ያለምንም ጥርጥር እነኝህን ድሎች ያገኛል፡፡ በመሆኑም ወያኔ ዐቢይ እዚያ እንዲገኝ የፈለገበት ምክንያትና ዓላማ እንዲህ ቀላል አይደለም፡፡ ከወቅታዊ ችግሩ አኳያ ከባድ ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ፋይዳና እንድምታ ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ለቀላል የሕዝብ ግንኙነት ፍጆታ አይደለም ወያኔ ዓይኑን በጨው አጥቦ ዐቢይ እዚያ መድረክ ላይ እንዲገኝ ጥያቄውን ያቀረበው፡፡

የፌዴሬሽኑ (የነጻ አሥተዳደሩ) የባለአደራ አባላት በአንዳች ነገር ካልተያዙ ወይም ካልተገዙ በስተቀር መተዳደሪያ ደንባቸውን ጥሰው ዐቢይን በመቀበል ቁማርተኛው ሸፍጠኛው ወያኔ በሜዳችን ላይ ነጥብ አስጥሎን ወይም አስቆጥሮብን እንዲወጣ ያመቻቻሉ ይፈቅዳሉ የሚል እምነት አይኖረኝም፡፡ ጉዳዩ ለወያኔ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ለማስረዳት ሞክሬያለሁ፡፡ ይሄ ምን ማለት እንደሆነ ይገባቸዋል ብየ እገምታለሁ፡፡ ከመሰብሰባቸው በፊት ይሄንን ጽሑፍ የጻፍኩትም ለዚሁ ነው፡፡ ከግንዛቤ ጉድለት አኳያ ከተሳሳተ ውሳኔ ላይ እንዳይወድቁ ለመታደግ፡፡ የባለአደራ አባላትን የምታውቋቸው ወገኖች ተሰብስበው ከመወሰናቸው በፊት ይሄንን ጽሑፍ እንድታደርሷቸው እጠይቃለሁ፡፡

እናም የዐቢይ እነዚያ ቦታላይ መገኘት የሚጠቅመው ወያኔን ብቻ ነው፡፡ ለሕዝብ ግን ዐቢይ እዚያ ተገኝቶ መለፈፉ ምንም የሚፈይድለት ነገር ስለሌለ የባለአደራ አባላቱ "ለሕዝብ ጥቅም ብለን ነው!" ብለው ሊጠቅሱት የሚችሉት አንድም ጥቅም ስለሌለ በሕዝብ ጥቅም በማመሃኘት ሊፈቅዱ አይችሉም አይኖርባቸውምም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበቃውን ያህል ከዚያም በላይ የዐቢይን ልፈፋ ጠጥቶ ጠግቧል፡፡ ሌላ ተጨማሪ ልፈፋ መስማት አይደለም አሁን የሚፈልገው፡፡ ተግባር ነው አሁን ማየት የሚፈልገው፡፡ ፌዴሬሽኑ (ነጻ አሥተዳደሩ) የዶ/ር (የሌ.ማ.) ዐቢይን ጥያቄ የማይቀበለው ከሆነ በሚሰጠው ምላሽ ይሄንን የሚከተለውን ቢል ደስ ይለኛል፡-

"ጠቅላይ ዋና ሹም ዶ/ር (ሌ.ማ.) ዐቢይ አሕመድ ሆይ! በቅድሚያ ለፌዴሬሽኑ (ለነጻ አሥተዳደሩ) ክብር ሰጥተው ጥያቄውን በማቅረብዎ ላቅ ያለ ክብርና ኩራት ይሰማናል፡፡ ሕዝቡን ፊትለፊት አግኝተው ንግግር ለማድረግና ከሕዝቡ ጋር ለመግባባት ያለዎትን

ከፍተኛ ፍላጎት እንረዳለን፡፡ ይሁንና ግን 1ኛ. የመተዳደሪያ ደንባችን የሚከለክል በመሆኑ፡፡ 2ኛ. ዳያስፖራው (ግዩራኑ) የሀገሩን ጉዳይ በንቃት የሚከታተል እንደመሆኑ እርስዎ በየ ክፍለሀገሩ (ክልሉ) እየዞሩ ያደረጉትን ንግግርና ውይይት በጥሞና ተከታትሏል፡፡ ዳያስፖራው (ግዩራኑ) በነዚያ ንግግርና ውይይት ባደረጉባቸው መድረኮች ከተነሡት ቁምነገሮችና የሕዝብ ጥያቄዎች የተለየ ጥያቄና ፍላጎት የሌለው ስለሆነ እዚህ እንዲገኙ ፈቅደን ውድ ጊዜዎትንና የሀገርን ውድ የውጭ ምንዛሬ ማባከን አልፈለግንም፡፡ በእርግጠኝነት ልናሳውቅዎ የምንፈልገው ጉዳይ ግን ለቃልዎ ታምነው ለሕዝብ የገቡትን ቃል ተግብረው የተናገሩትን ለውጥ ማምጣት ከቻሉ ያኔ በሕዝባችን መሀል ያለው የጥልና የልዩነቱ ግንብ ስለሚፈርስና እንደ አንድ ሀገር ሕዝብ አንድ ብሔራዊ መግባባት ላይ ስለምንደርስ "ደንባችን ይከለክለናል!" ሳንል በሚቀጥሉት የውድድር ዘመናት ወይም በዓላት እርስዎ ሳይሆኑ እኛ ራሳችን በክብር ጋብዘን በታላቅ ድምቀት የምንቀበልዎ መሆኑን በአክብሮት ልንገልጽልዎ እንፈልጋለን፡፡ እኛና እርስዎ በዚህ መድረክ መገናኘት ካለብን ትክክለኛ ሰዓቱ ለሕዝብ የገቡትን ቃል መፈጸምዎ ከታወቀ በኋላ እንጅ አሁን አይደለምና በጠቀስናቸው ምክንያት ጥያቄዎትን ባለመቀበላችን ይቅርታ እየጠየቅን ትኩረትዎን ወደ ተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ እንጠይቃለት!" ብሎ ባለአደራው መመለስ ይኖርበታል፡፡

ነገር ግን ይሄ ሳይሆን ቀርቶ የባለአደራ የአሥተዳደር አባላቱ ክህደት ፈጽመው ዐቢይ እንዲገኝ ከፈቀዱ ግን ዳያስፖራው (ግዩራኑ) በበዓሉ ወይም በዝግጅቱ ቦታ ባለመገኘት ተቃውሞውን እንዲገልጽና ብዙ የደከመበትንና ፍሬም እያፈራ ያለውን የተቃውሞ ትግሉን ከኪሳራ እንዲታደግ ከወዲሁ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ ከበዓሉ በኋላም እነኝህን ክህደት የፈጸሙ የባለአደራ አባላትን የማስወገዱንና በታማኝ የሕዝብ ልጆች የመተካትን እንቅስቃሴ ወዲያውኑ መቀጠል ይኖርበታል እላለሁ፡፡ ፌዴሬሽኑ የሕዝብ ነኝ ካለ መቸም ቢሆን ከሕዝብ ጎን ሊቆም ይገባል! ከሕዝብ ጎን ካልቆመ ግን የሕዝብ አይደለም! የሕዝብ እንዲሆን ሕዝቡ ይንቀሳቀሳል!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com